የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር
Ministry of Science and Higher Education - Ethiopia

# የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች የዲስፕሊን መመሪያ

(መመሪያ ቁጥር፡ ሳከትሚ/002/2012)

የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር
መስከረም 2012 ዓ.ም
አዲስ አበባ

## ክፍል ሁለት
## መብቶችና ግዴታዎች

በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 1152/2011 በአንቀጽ 38ና 39 የተዘረዘሩትን እንዳሉ ሆነው በተጨማሪ የተማሪዎች መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ክፍል ቀርበዋል፡፡

**አንቀጽ 5፡- የተማሪዎች መብቶች፣**

1. በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ሴኔት ባወጣው የትምህርት የጊዜ ሠሌዳ መሠረት በነጻነት የመማር፣ የመጠየቅ፣ የመመራመር፣ የመረዳዳት፣ የማወቅ፣ ሳይንሳዊና ጥበባዊ ክህሎትን የማሳደግ፣ ልቀ መገኘት፣
2. በመማሪያ ክፍል፣ በዩኒቨርሲቲ ግቢና በህብረተሰቡ ውስጥ ለመማር አመቺ ሁኔታን የማግኘትና የመጠቀም፣
3. በዩኒቨርሲቲ ግቢ ውስጥ ህገ-መንግስታዊና ሰብዓዊ መብታቸውና ደህንነታቸው ተጠብቆ የመኖር፣
4. በዩኒቨርሲቲ ጉዳዮች ላይ በህጋዊና በሰላማዊ አግባብ አቋማቸውን በነጻነት የማራመድ፤
5. ማንኛውንም አይነት አድሎ ወይም ትንኮሳ እንዳይደርስባቸው ህጋዊ ከለላን የማግኘት፤
6. በማንኛውም የመምህርና የተማሪ ግንኙነት የፍትህና ፍትሃዊነት ተጠቃሚ የመሆንና ለመማር የሚያነሳሳ መልካም ተቋማዊ ድባብን የማግኘት፤
7. ስለአካዳሚያዊ ብቃታቸው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ በተደነገጉ መርሆዎችና በዩኒቨርሲቲው አካዳሚክ መመዘኛዎች መሰረት የመመዘን፣ ኢ-ፍትኃዊ ምዘና ሲፈጸም ቅሬታን በዩኒቨርሲቲው ስርዓት መሠረት በሰላማዊና ህጋዊ መንገድ የማቅረብና ፍትሕን የማግኘት፤
8. ግልጽነት ባለው ስርዓት መሠረት የመምህራንንና ሌሎች አካዳሚክ ሰራተኞችን የስራ አፈጻጸም መሙላትና የአፈጻጸም ግምገማው ላይ በመሳተፍ አስተያየት የመስጠት፣
9. በትምህርት ማህደራቸው ዉስጥ የሚቀመጡ መረጃዎች በሚስጢር ስለሚጠበቁበትና ለሌላ ወገን ስለሚገለጹበት ሁኔታ የሚወስን አስማማኝ ስርዓት ተጠቃሚ የመሆን፣
10. የተማሪው የጋራ ጥቅሞችን በህጋዊ መንገድ እንዲጠበቁ ለማስቻል አግባብነት ባላቸው ህጎች በተቋቋመና የዩኒቨርሲቲውን ተማሪዎች በሙሉ በአባልነት በሚያቅፈው የዩኒቨርሲቲው የተማሪዎች ህብረት አባል የመሆን፣
11. በዩኒቨርሲቲው ደንብና ስርዓት መሠረት በግልም ሆነ በማህበራቸዉ አማካይነት በዩኒቨርሲቲው መገልገያዎች የመጠቀም፤
12. በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ድንጋጌዎችና የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ቦርድ በሚያወጣቸው መመሪያዎች መሠረት በማህበራቸው ወይም በተወካዮቻቸው አማካኝነት በተለያዩ የዩኒቨርሲቲው አካደምያዊና አስተዳደራዊ ስብሰባዎች ላይ የመሳተፍ፤
13. የፈተና ውጤትን በወቅቱ የማየት፣ ቅሬታ ካለ የማቅረብ
14. የፈተና ውጤት /Grade Report/ በወቅቱ የመቀበልና አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎች በማቅረብ አግባብነት ያለው የትምህርት ማስረጃ በጊዜ የማግኘት፣
15. የየሴሚስተሩን የመጨረሻ የፈተና ፕሮግራም በቂ በሆነ ጊዜ (ቢያንስ ከአንድ ሳምንት በፊት) የማወቅ፣
16. ማንኛውም መደበኛ ተማሪ የወጭ መጋራት ውል ከፈረመ ወይም ለአገልግሎቱ የሚገባውን ክፍያ በቅድሚያ እስከ ፈፀመ ድረስ ዩኒቨርሲቲው የሚሰጠውን የምግብ፣ የመኝታ፣ የህክምናና የመዝናኛ አገልግሎቶችን የማግኘት፣
17. ከትምህርት ጋር አግባብነት ያላቸውን ሀሳቦች የማቅረብ፣ የመከራከርና የመወያየት፣

ግድፈቶች የዲሲፕሊን ማንኛውም ለሚፈጠሩ ጋር ማህበረሰብ
18.ከዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ጋር ለሚፈጠሩ ማንኛውም የዲሲፕሊን ግድፈቶች (አለመግባባቶች) አግባብነት ያለው ፍትህ የማግኘት እና በተገቢው አካል የመዳኘት፣

19.በዩኒቨርሲቲው ውስጥ በሚቋቋሙ የተማሪዎች ክበባትና ሌሎች አግባብነት ባላቸው አደረጃጀቶች (ለምሳሌ የመኝታ ቤት፣ የመኖሪያ ሕንፃ፣ የዲስኘሊን፣ የመዝናኛ፣ የምግብ ቤት፣ የፀረ-ኤድስ፣ የጤና፣ የአካባቢ፣ የስፖርትና የመዝናኛ ወዘተ) ውስጥ በአመራርነት ሆነ በአባልነት የመሳተፍ፣

20.በዩኒቨርሲቲው የሚሰጡ አገልግሎቶች በእኩልነትና በፍትሃዊነት የማግኘት፣

21.በዩኒቨርሲቲው ህገ ደንብ /Legislation/ የተካተቱትን መብቶች በአግባቡ የመጠቀም፡

22.በጥፋተኝነት በሚከሰሱበት ጊዜ የተከሰሱበትን ወይም የተጠረጠሩበትን ጉዳይ በተመለከተ የበኩላቸውን ማስረጃና ክርክር የማቅረብ፣

23.በአካዳሚክና በአስተዳደራዊ ነክ ጉዳዮች ዙሪያ በሰላማዊ ሁኔታ የመወያየትና ሐሳብ የመስጠት ብሎም ፓናል ውይይት የማዘጋጀት፣

24.በሥራቸውና በችሎታቸው መሰረት ያለ ምንም አድልዎ የመገምገምና የግምገማ ውጤታቸውን የማወቅ፣ ቅሬታ ካላቸውም ስርአትን ተከትሎ የፈተና ወረቀቶቻቸውና የተገመገሙባቸው ስራዎቻቸው እንደገና እንዲታይላቸው የማመልከት፣ ውጤቱንም የማወቅ፣

25.በዩኒቨርሲቲው ህገ ደንብ (Legislation) መሰረት በማንኛውም የመማር ማስተማርና አገልግሎት በሚሰጥበት መስክ በብሄር፣ በጾታ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ ወይም በሌላ ወገንተኝነት ምክንያት አድልዎ የማይደረግባቸው መሆኑን መረዳት፣ ከተደረገባቸውም ለሚመለከተው የአመራር አካል ቅሬታቸውን የማቅረብና ምላሽ የማግኘት፣

26.የምግብ አገልግሎት ከዩኒቨርሲቲው የማይፈልጉ ተማሪዎች ማመልከቻ አቅርበው የሚመለከተው አካል ሲፈቅድ በወጪ መጋራት ደንብ መሰረት በወር ለምግብ የተበጀተውን ገንዘብ የመውሰድ መብት

27.ቤተ ሙከራዎችና ወርክሾፖች እንዲሁም ሌሎች ትምርታቸውን ሊያግዙ የሚችሉ የዩኒቨርሲቲውን ወይም የሌሎች ተቋማትን በሚመለከተው አካል ክትትል የመጠቀም መብቶች አሏቸው፡፡

**አንቀጽ 6፡- የተማሪዎች አጠቃላይ ግዴታዎች፣**

1. ትምህርት ይጀመራል በተባለው የጊዜ ገደብ በዩኒቨርሲቲው በአካል ተገኝቶ የመመዝገብና ትምህርት ይጀመራል በተባለው የጊዜ ገደብ በዩኒቨርሲቲው በአካል ተገኝቶ የመመዝገብና በክፍል የመገኘትና አስፈላጊውን ፎርማሊቲዎች አሟልቶ ትምህር የመጀመር፣ ትምህርቱን በሚገባ የመከታተል፣
2. የከፍተኛ ትምህርት ዓላማዎችንና የዩኒቨርሲቲውን መሪ እሴቶች የማወቅና የማራመድ፣
3. አግባብነት ያላቸውን የሀገሪቱን ህጎች፣ የዩኒቨርሲቲውን የተማሪዎች ዲስፕሊን መመሪያ፣ የተቋሙን የሴኔት ደንብ እንደዚሁም ሌሎች ተፈፃሚነት ያላቸውን ህጎች የማወቅ፣ የማክበርና የማስከበር በነሱም የመመራት
4. ከማንኛውም ማህበረሰብ ጋር በሚኖረው ግንኙነት ሕገ-መንግስታዊ መብቶቻቸውን የማክበር፣
5. የግልም ሆነ የጋራ የተማሪዎች ጥቅም አደጋ ላይ በሚወድቅበት ጊዜ ፍጹም ሰላማዊና ሕጋዊ በሆነ መንገድ ቅሬታን በማሰማት በጋራ መፍትሄ የመሻት፣
6. የዩኒቨርሲቲውን የጋራም ይሁን የግል መገልገያ ንብረት በጥንቃቄ የመያዝና የመጠቀም፣ ሆን ተብሎ ወይም በቸልተኝነት ምክንያት በዩኒቨርሲቲው ንብረት ላይ ለሚደርሰው አደጋና ለሚከሰተው ማንኛውም ጉዳት በጋራም ሆነ በግል ተጠያቂ

የመሆን፣ እንደዚሁም የደረሰውን ጉዳት የመተካት፤ ጥፋት ያደረሰውን አካል የማጋለጥ፤

7. ዩኒቨርሲቲው ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች መከፈል የሚገባውን ክፍያ የመፈፀም፤
8. ሁልጊዜ የመገልገያ/የመታወቂያ ካርድ መያዝና ለሌላ አካል አሳልፎ አለመስጠትና በሚመለከተው አካል ሲጠየቁ የማሳየት፣
9. በተመዘገቡበት የትምህርት መስክ የተቀመጡ የብቃት መመዘኛዎችን ማሟላት፣ የላቦራቶሪ ሪፖርቶችን እና ሌሎች በመምራን የተሰጡ ሥራዎችን በወቅቱ አጠናቆ ማስረከብ፣
10. በልዩ ሁኔታ ካልተፈቀደ በስተቀር ለእያንዳንዱ የትምህርት ኮርስ (ዓይነት) በሚወጣው ኘሮግራም መሰረት በሌክቸር፣ በላቦራቶሪ፣ በወርክሾፕና በመስክ በመገኘት ትምህርቱ የሚጠይቀውን ተግባራትን የማከናወን፣
11. በዩኒቨርሲቲው የተደነገገውን የምሽት መግቢያና መውጫ ሰዓት ማክበር፤
12. ማንኛውንም መምህር፣ የአስተዳደር ሰራተኛ እንዲሁም የመማር ማስተማርንና የአስተዳደር ሂደቱን የመምራትና የመቆጣጠር ኃላፊነት ያለውን አካል የማክበር፣
13. ሰልፍ ባለበት ቦታ ሁሉ ሰልፍን ጠብቆ መገልገል፣
14. በማንኛውም ጊዜ ግቢውን ሲለቁ የተረከቡትን ንብረት በአግባቡ ቆጥሮ ማስረከብ፣ ክሊራንስ በማውጣት ግቢውን በወቅቱ መልቀቅ፣
15. ሱስ ከሚያስይዙ (ጫት፣ ሲጋራ፣ አልኮል፣ ሺሻና የመሳሰሉት) ጎጂ ልማዶች ራስን መጠበቅ፣
16. በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የወጪ መጋራት ደንብ መሰረት ለትምህርትና ለአገልግሎት ተገቢውን ክፍያ መክፈል ወይም የወጪ መጋራትን ውል መፈረም፣
17. ከዩኒቨርሲቲው ካምፓስ ውጪ ካለው ማህበረሰብ ጋር በሚኖረው ግንኙነት በመልካም ስነ-ምግባር አርአያ መሆን፣
18. የሌላውን ባህል፣ ቋንቋ፣ ሃይማኖት፣ ወዘተ ማክበርና መጠበቅ፣
19. ከማንኛውም ሕጉ-ወጥና ከስነ-ምግባር ውጭ ከሆኑ ተግባራት የመቆጠብ፣ ለምሳሌ ከስርቆት፣ አላግባብ በመጮህ ሌላውን ከማወክ፣ ለሕገ-ወጥ ተግባር ሌሎችን ከማነሳሳት፤ ሱስ ከሚያስይዙ (ጫት፣ ሲጋራ፣ አልኮል፣ ሺሻና የመሳሰሉት) ጎጂ ልማዶች ... ወ.ዘ.ተ ራስንና ሌሎችን የመጠበቅ፤
20. አንድ ተማሪ በተለያዩ ምክንያቶች መባረሩን ሲያውቅ ሰበብ አስባብቦ ፈልጎ ሌላውን ተማሪ ይዞ ለመጥፋት ያልሆኑ ጥያቄዎችን ማንሳት፣ ሌሎችንም ቀስቅሶ ረብሻ ለመፍጠር መሞከር፣ በማንኛውም ምክንያት ከሌሎች ጋር መጣላትና የመሳሰሉትን ችግሮች ስለሚፈጥር እንደዚህ ዓይነት ተማሪዎችን ለሚመለከተው አካል ጥቆማ በመስጠት በጊዜ መፍትሄ እንዲፈለግላቸው የማድረግ፣
21. ማንኛውም ተማሪ ከዶርሚተሪው ውጭ ሄዶ ያለመተኛት፣ ሌላ ተማሪም አስደርቦ አለመገኘት፣ ያለፈቃድ የመኝታ ክፍል አለመቀያየር
22. በመኝታ ቤት ምንም ዓይነት ተቀጣጣይ ነገሮችን ያለመያዝ፣ ምግብ ማብሰልና ካውያ አለመጠቀም እና ምንም አይነት ሰው ሊጎዳ የሚችል መሳሪያ ይዞ አለመገኘት፣
23. በሁለት ተማሪዎች መካከል የሚነሱ ግላዊ ጥሎችን ወደ ብሔርና ሃይማኖት በመለወጥ ግጭት ውስጥ አለመግባት፣
24. የሚሰጡ የትምህርት የተለያዩ ሥራዎችን በራስ ጥረት መሥራት፣ የሌላ ሰው ሥራ የራስ አስመስሎ አለማቅረብ፣ ለሌላ ሰው ሠርቶ መስጠት ወይም ከሌላ ሰው መውሰድ ወይም መኮረጅ የማይቻልና ዋጋ የሚያስከፍል መሆኑን የመረዳት፤